# በብርቱና ባስቸኳይ መወገዝ ያለበት አዲሱ የሃዋርያት እንቅስቃሴ
# NEW APOSTOLIC REFORMATION

በዶ/ር ቴዎድሮስ አየለ

ውድ የክርስቶስ ቤተሰቦች ስለዚህ የአዲሱ ሃዋርያት እንቅስቃሴና ስለሌሎችም በዚህ በመጨረሻው ዘመን በተለይ ከባህር ማዶ ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ ስላሉቱና ሊገቡ ስላሰፈሰፉቱ አንዳንድ እግዚአብሄራዊ ስላልሆኑ የክህደት ትምህርቶች kendemeleket.com በሚል አዲስ ድረ ገጽ ላይ ለማውጣት በዝግጅት ላይ ሳለሁና በኢትዮክሮስ www.ethiocross.com/blogs ገጾች ላይ በቅርቡ ስለዘመኑ ሃዋርያት እንቅስቃሴ አንዳንድ መጣጥፎችና ምልልሦችን ስላየሁ ፤ ለአንባቢያን ትንሽ ብርሃን ይፈነጥቃል ብዬ ስላመንኩ ለድረገጻችን ያዘጋጀሁትን ጽሁፍ ትንሽ ራገፍ ራገፍና አንዳንድ የሚያስፈልጉ ነገሮችን አክል በማድረግ ለዚህ ብሎግ ታዳሚዎች ይህንን ጽሁፍ ይዤ ቀርቤአለሁ።

ውድ ኢትዮጵያውያን የጌታ ቤተሰቦች ፤ በተለይም ጌታ ኢየሱስ በደሙ የዋጃትን የኢትዮጵያን ህዝበ ክርስትያን የምትወዱና የምትመግቡ መሪዎች ይህንን አዲሱን የሃዋርያት እንቅስቃሴ (The New Apostolic Reformation) የሚባለውን የክህደት እንቅስቃሴ እጅግ በብርቱና ባስቸኳይ እንድትቃወሙት እንዲሁም እንድታወግዙት በክርስቶስ ፍቅርና በሰው ልጅ መንፈሳዊ ህልውና እለምናለሁ። በተጨማሪም ልዩ ልዩ የክርስትያን ሚዲያ አገልግሎቶች በዚህ ጉዳይ ላይ የጉዳዩን አሳሳቢነት ተገንዝባችሁ ምእመኑ ከዚህ እንቅስቃሴ እንዲርቅ ታሳውቁ ዘንድ እለምናለሁ።

## ይህ እንቅስቃሴ በሃገራችን በኢትዮጵያ

ይህም እንቅስቃሴ በሃገራችን በኢትዮጵያ እንዲሁም በውጪ አገር በሚገኙ የኢትዮጵያ የክርስቶስ ማህበሮች ማረፊያ አግኝቶ ከረገጠ ሰንበትበት ማለቱን በቅርቡ ባገኘናቸው መረጃዎች ልናውቅ ችለናል። ይህ እንቅስቃሴ ወደሃገራችን እየገባ ያለው በአንድ ሃዋርያ ብቻ ሳይሆን ከሶስትና ከአራት በላይ በሚሆኑ መሪዎች ያውም የብዙ ቤተክርስትያኖች ተጠሪዎች በሆኑ አማካኝነት ነው። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ስም ዝርዝራቸውን ወደፊት አስታውቃለሁ።

በተጨማሪም በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ያላችሁ እንዲሁም ደግሞ ከዚህ ከአዲሱ የሃዋርያት እንቅስቃሴ ጋር አብራችሁ ለመስራት የምታስቡ ውድ ወገኖች ሆይ እባካችሁ ይህን ጽሁፍና ሌሎችንም ስለ እዚህ እንቅስቃሴ የተጻፉ ጽሁፎችን በማንበብ እንዲሁም በጸሎት ነገሩን ተመልክታችሁ ምናልባት ከዚህ በፊት ስለዚህ እንቅስቃሴ ምንነት ያላያችሁትን መጥፎ ጎኑን እዚህ ጽሁፍ ውስጥ ካስተዋላችሁ ከዚህ እንቅስቃሴ በብርቱና ባስቸኳይ እንድትሸሹና እንድትለዩ ጥሪ አቀርባለሁ።

## ስለእኔ ማንነት

ሌላው ስለእኔ ማንነት ትንሽ ለመናገር ያህል ፤ እኔ በአሁኑ ግዜ በአሜሪካን አገር ቤተሰብ መስርቼ የምኖር ፤ የጌታ ኢየሱስን የግል አዳኝነት የማምን እንዲሁም የእግዚአብሄር ቃል ለክርስትያን በሙሉ የመጨረሻ ስልጣን አለው ብዬ የማምን ወንድም ነኝ። መቼም እግዚአብሄር ውጪ በሚኖር ሰው ለኢትዮጵያ አይናገርም ብላችሁ እንደማትሉ ተስፋ አደርጋለሁ። ለኢትዮጵያውያን ጌታ እንኳን በኢትዮጵያዊ ከፈለገ በአህያም እንደሚናገር ቃሉ ስለሚያስተምረን ስለዚህ ጆሮአችሁን ስጡኝ ለማለት ያህል ነው።



www.Ethiocross.com

ይህን ያህል ለመንደርደሪያ ከተናገርኩ እስኪ እንግዲህ ከዚህ በመቀጠል ስለ እንቅስቃሴው መሰረ አላማ ከራሳቸው በተለይም የዚህ እንቅስቃሴ መሪ ከጻፋት መጽሃፍት በመነሳት የዚህን እንቅስቃሴ የስልጣን ጥምና መጽሃፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ አሰፈሪ አካሄድ እንመልከት።

## የእንቅስቃሴው መሪና መስራች

እንደ እንቅስቃሴው መሪና መስራች ዶር ፒተር ዋግነር (Peter Wagner) አገላለጽ ይህ እንቅስቃሴ የበሰለውና ታላቁን ተልእኮ ማከናወን የጀመረው በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ 2001 አ.ም. ነው። ዶ/ር ዋግነርም Dominion! በሚለው መጽሃፋቸው እንዲህ ይላሉ፦ In a word, we are now in the Second Apostolic Age. We have been here to the best of my calculation, since around 2001[1]. "በአንድ ቃል ለመናገር ያህል በአሁኑ ሰአት በሁለተኛው የሃዋርያት ዘመን ላይ እንገኛለን። እንደ እኔ ስሌት መሰረት እዚህ ዘመን ውስጥ ከ 2001 አ.ም. ጀምሮ ገብተናል" ይላሉ። የዚሁ እንቅስቃሴ ሌላ ጥምር አካል ስለሆኑት ስለነቢያቱ በድረገጻችን ላይ ወይም በኢትዮክሮስ ብሎግ ላይ ወደፊት እንገልጻለን (በጥምሩ የሃዋርያትና የነቢያት እንቅስቃሴ - The Apostolic and Prophetic Movement በመባል ይታወቃሉ። አዲሱ የሃዋርያት እንቅስቃሴ በክርስቶስ ኢየሱስ ቤተክርስታያኑን ለመመስረት ስልጣንና ሃላፊነት በድሮ ጊዜ እንደተሰጣችው እንደ ቀደሙት የበጉ ሃዋርያት እንደ እነ ጴጥሮስና ዮሃንስ በዚህ ታሪክ መጠቅለያ በሆነው በአሁኑ ዘመን ደግሞ ለቤተክርስትያን እኛ አሁን በምድር ላይ መሪዎችዋና መሰረት ነን ባይ ናቸው።

የሃዋርያነትን ጥሪ ለማጽደቅና የትኛው ሰው ሃዋርያ መሆን እንደሚገባው ሲያሳስቡ Apostles of the City በሚለው መጽሃፋቸው ዶር ፒተር ዋግነር እንዲህ ይላሉ፦ But out of all the local church pastors in a city, the most likely segment among them to be seen as a pool for identifying apostles of the city would be mega church pastors[2] "በከተማ ውስጥ ካሉት አጥቢያ ቤተክርስትያኖች ውስጥ የከተማ ሃዋርያት ሊገኙ የሚችሉት በከተማው ውስጥ ካሉ ብዙ አባላት ካሏቸው ትልልቅ ቤተክርስትያን መሪዎች ውስጥ ነው" ይላሉ።

በሌላ ቦታ በዚሁ መጽሃፍ ላይም የአንድ ከተማ መጋቢዎች (ፓስተሮች) እንዴት በሃዋርያ ስር መሆን እንደሚገባቸው ሲናገሩ፦ The other pastors in the City function under the apostles as church staff members would ordinarily function under their senior pastor[3] "በከተማው ውስጥ ያሉ መጋቢዎች ልክ እንደ ቤተክርስትያን ቅጥር ሰራተኞች በሃዋርያቱ ስር መሆን አለባቸው።" ደግሞም እንደገና በሌላ ቦታ እዚሁ መጽሃፍ ላይ፦ The Apostle would be mentoring the pastors. The apostle holds the pastors accountable[4] "ሃዋርያው መጋቢዎቹን ማሳደግና መቆጣጠር አለበት" ይላሉ።

እነዚህ የአዲሱ ሃዋርያ እንቅስቅሴ አመራር አባላት በአሁኑ ሰአት ወደ 500 ይደርሳሉ፤ The International Coalition of Apostles በመባልም ይታወቃሉ (ዝርዝራችውን ለማግኘት ይህንን የራሳቸውኑ ድረ-ገጽ http://www.apostlesnet.net/members.htm ይጎብኙ። እነዚህ የተመረጡት ሃዋርያቶች መካከል ለመግባት ከእነርሱው በአንዱ ጥቆማ ካልተደረገና ካልተጠሩ በስተቀር ማንም ሊገባ አይችልም። እንግዲህ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ ተመርጠው 25 ያህል የሚሆኑቱ እየተመካከሩ ራእይ አርቃቂዎችና አስፈጻሚዎች ደግሞ The New Apostolic Roundtable[5] በመባል ይታወቃሉ።



www.Ethiocross.com

ከዛ የስልጣኑ ተዋረድ ይቀጥልና የሁሉም ሃዋርያት የጊዜው ሰብሳቢ ሃዋርያ ለሁሉ ነገር የማሰሪያ ቃል ያለክርክር ይሰጣል ፤ ይናገራል እንዲሁም ይፈርዳል። ይህንንም ዶ/ር ፒተር ዋግነር በመጽሃፋቸው[6] ላይ ሃዋርያው ያእቆብ በኢየሩሳሌም በተደረገው የሃዋርያትና የሽማግሌዎች ስብሰባ ላይ (የሃዋርያት ስራ 15፥13-20) የመጨረሻ ቃል እንደሰጠ እንዲሁ የሁሉ የበላይ የሆነው የአዲሱ ሃዋርያት እንቅስቃሴ መሪም እንዲሁ እንደ ያእቆብ ስልጣን እንዳለው ይናገራሉ። ነገሩ የካቶሊክ ጳጳሳት ስለቤተክርስትያን ትምህርት በሚናገሩበት ጊዜ ስህተተ - ቢስ እንደሆኑ እንደሚያስተምሩቱ ይህም የአዲሱ ሃዋርያ እንቅስቃሴ አሰራር እዚህ ጋር እንደካቶሊኮቹ ይመስላል።

ለመሆኑ ለዘመኑ ሃዋርያት እውቅና መስጠትስ ካስፈለገ በሀሩር፤ በብርዱ፤ በግርፋት፤ በእርዛት፤ በመራብ፤ በመጠማት ሰው ባልደረሰባቸው ቦታ ሄደው ፤ የቀደሙቱ ሃዋርያት (የበጉ ሃዋርያት) ካስተማሩን ከቃሉ ቅንጣት ታክል ፍንክችና ፈቀቅ ሳይሉ ለወንጌል ደማቸውን እስከማፍሰስ ደርሰው እንደጌታቸው እስከሞት ድረስ ራሳቸውን ለሰጡት ሰዎች እውቅና መስጠት አይገባንምን? ቤተክርስትያንን መትከልም ብቻ ሳይሆን እንደ እነዚህ ያሉት ሰዎች ለዳኑት ሰዎች ካላቸው የጠለቀ ፍቅር የተነሳ እንደሃዋርያው ጳውሎስ "ስለዚህ ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በእንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሠጽ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትጉ" (የሐዋርያት ሥራ 20፥31) እንዳለው ፤ ቅሌን ጨርቄን ሳይሉ እዚያው ቤተክርስትያን የተከሉበት ቦታ ሆነው ፤ ቅዱሳኑን በክርስቶስ ትምህርት ያጸኑትን ቢያስፈልግ ሃዋርያት ልንል በተገባን ነበር።

ሃዋርያ የሚባለው ፤ ምናልባት እራሱ በላቡና በደሙ ያፈራቸው ቤተክርስትያኖች ላይ ፍርሃት በተሞላበትና መጽሃፍ ቅዱሳዊ በሆነ አሰራር እልቅና ሊኖረው ይችል ይሆናል ፤ ከዛ በላይ ግን ስልጣን ሊኖረው እንዴት ይገባል? ሃዋርያው ጳውሎስም በዚህ ምክንያት በሰው መሰረት ላይ እንዳልሰራ ወንጌል ባልተነገረበት ቦታ ወንጌልን ልሰብክ ተጣጣርኩ (ሮሜ 15፥20) ይላል።
እንደ ዘመኑ ሃዋርያት በገንዘብ ሃይል፤ በዝናና እንዲሁም በመሳሰሉት ምክንያቶች በማባበል ፤ ሌላው በተከለውና ባሳደገው ላይ አለቃና ባለስልጣን ለመሆን መፈለጉ ፈጽሞ ስነ-ምግባር የጎደለውና መጽሃፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ነው።

እነዚህ በአሁኑ ሰአት በአለም ላይ እየመሩ ያሉ ሃዋርያ ነን ባዮች ሁሉን ነገር በስራቸው ሊያደርጉ ያሉ ፤ ባለማወቅ የስንቱን ፍርድ ይሸከሙት ይሆን? ሰው ስራ ውስጥ ገብቶ ወዲያ ወዲህ ማለት በራስ ላይ የእሳት ማገዶ መከመር ነው። ለሌላው ቤተክርስትያን ያውም እነርሱ እንደሚያደርጉት ለአለም ሁሉ ቤተክርስትያናት እቅድ ከማውጣት ይልቅ ለጊዜው እራሳቸው የተከሏቸውን ቤተክርስትያናት እንኳን በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በቅጡ በያዙት። የቤተክርስትያን ጉዳይ የታላቁ አምላክ ስራ እና የህይወት ጉዳይ ነውና። በጌታም እጅ በፍርድ መውደቅ ደግሞ እጅግ ያስፈራል።

እነዚህ ግን አዲስ ሃዋርያ ነን ባዮች በሞቀ ወንበርና በጠረጴዛ ዙርያ እየተሰበሰቡ እንዴት ክርስትያኑን ብሎም አለምን የሚገዙበትን ስልት እያወጡና እያውጠነጠኑ ክፉኛ የስልጣን ጥም የያዛቸው ሌላው ተጋድሎ በደሙ ያቀመውን ለመንጠቅና ለመዝረፍ የሚያስፈስፉ ሃሰተኛ ሃዋርያትና ተኩላዎች ናቸው። እነዚህ ልክ አውሮፓውያን አፍሪካን በድሮ ጊዜ እንደቅርጫ ሲከፋፈሏት እንደነበረ እነዚህም የሃዋርያት መሪዎች በአሜሪካን ሃገር ቁጭ ብለው ትእዛዝ እየሰጡ ደግሞም ለሌሎቹ ሃዋርያት ከተማንና አገርን እንዴት እንደሚገዙና በእግራቸው ስር እንደሚያደርጉ እያስተማሩ ይገኛሉ። ደግሞም በዚሁ ስራ "ስራ ብዙ" የሆኑ ፤ ከጌታ ቃል ይልቅ ራሳቸውንና ስማቸውን ተክለው (legacy) ለማለፍ የሚያውጠነጥኑ ፤ የጌታን አሳብና ምክር ጥለውና ንቀው የራሳቸውን ለማቆም የሚሯሯጡ ደፋሮች ናቸው።



www.Ethiocross.com

## የአዲስ ሃዋርያት ትምህርት ከጌታ ቃል ጋር ማነጻጸር

እንግዲህ ይህን ያህል ስለአዲሶቹ ሃዋርያት የስልጣን ተዋረድና አንዳንድ ነገሮች ካየን ከዚህ በታች ደግሞ በመቀጠል ስለ እነዚህ አዲስ ሃዋርያት ትምህርት አንባቢው በቀላሉ መረዳትና ከጌታ ቃል ጋር ማነጻጸር እንዲችል አጠር ባለ መልኩ በሶስት ክፍሎች (ተራቁጥር) ውስጥ በማድረግ እንደሚከተለው አቀርባለሁ ፤

1. እነዚህ አዲስ ሃዋርያት ቤኤፌሶን 2፥20 "በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው" የሚለውን በእኛ በአሁኑ ዘመን ሃዋርያትና ነቢያትም ማለቱ ነው ብለው ይናገራሉ[7]። በጥምሩ የሀዋርያነትና-የነቢይነት አገልግሎት እንዳላቸው የሚነገርላቸውን ቢል ሀመን (Bill Hamon) የተባሉትን ሰው ፤ ዶ/ር ፒተር ዋግነር ጓደኛዬና በምድራችን ካሉ አንዱ ታላቅ ሰው ይሏቸዋል። ቢል ሀመን Apostles Prophets and the Coming Moves of God በሚለው መጽሃፋቸው ላይ የአሁኑን ዘመን ሃዋርያትና ነቢያት ከድሮ ዘመን ነቢያት ጋር እያነጻጸሩ በጻፉበት አንቀጽ ውስጥ ሁሉም በእኩል ሁኔታ አምላካዊ መገለጥ እንደተቀበል ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ፦ …this anointing for divine revelation was not just given to the prophets of old but has now been equally given to Christ's HOLY APOSTLES and PROPHETS in His Church.[8] "ይህ መለኮታዊ የመገለጥ ቅባት ለብሉይ ኪዳን ነቢያት ብቻ ሳይሆን በቤተክርስትያን ውስጥ ለቅዱሳኑ ለክርስቶስ ሃዋርያትና ነቢያትም **በእኩልነት** ደረጃ ተሰጥቷል" ይላሉ።

እስኪ አሁን ጌታ ኢየሱስ እና ሃዋርያቱ መሰረት ጥለው ካለፉ ከ 2000 አመት በኋላ ተነስቶ ለማሳሳት ካልሆነ በስተቀር ፤ አሁን መሰረት ነን ማለት ለምን አስፈለገ? የጌታ መንፈስ ለ 2000 አመት የሰራው ቤት ያልተሟላ መሰረት ላይ ስለነበረ ከንቱ ሆኗላ? መቼም መንፈስ ቅዱስ እስካሁን እውነተኛ አማኞችን በሃዋርያቱ ትምህርት አማካኝነት ማለትም በክርስቶስ ላይ ለእግዚአብሄር መኖሪያ የሚሆኑትን ሰዎች ሲሰራና ሲያፈራ እንደቆየ ማንም ሊክደው አይችልም።

እነዚያ የድሮዎቹ የክርስቶስ ሃዋርያት የኤፌሶን መጽሃፍ እንደሚነግረን ምንም እንኳን ቢሞቱም ለቤተክርስትያን ስጦታ እንደመሆናቸው መጠን (ኤፌሶን 4፥8) እስካሁን ድረስ ያውም ጌታ እስኪመጣና ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ ባኖሩልንና በተውልን ቃል መሰረት ቤተክርስትያኑን ይሰራሉ፤ ያርማሉ፤ ያቃናሉ፤ መንገድንም ያሳያሉ። እነዚህ የአዲሱ ሃዋርያት እንቅስቃሴ መሪዎች የቤተክርስትያን አስታጣቂ ነን ፤ ቤቱን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብረን እንሰራለን በማለት ፈንታ ኤፌሶን 2፥20ን በመጥቀስ መሰረት ነን ለማለት እንዴት ይደፍራሉ? አዲስ መሰረት ሊመሰርቱ ካልሆነ በስተቀር።

መቼም በሃዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች ላይ እንደምናየው የክርስቶስ ሃዋርያት በነበሩበት ግዜ ሃሰተኛ ሃዋርያትና ክፉ ሰዎች የሃዋርያውን ጳውሎስ ሃዋርያነት ሲፈታተኑ እንደነበረ ፤ እነዚህ አዲሶቹ ሃዋርያት ደግሞ እንደድሮዎቹ ሃሰተኛ ሃዋርያት ቃሉን እየተፈታተኑ እንደ ጳውሎስ መሰለው መገኘትን ይፈልጋሉ። ሌሎቹን 12ን የጌታ ሃዋርያትማ መሆን አይችሉም ፤ ምክንያቱም የጌታ **መስራች** ሃዋርያ ለመሆን ጌታን እዚህ በምድር ላይ በስጋ በነበረ ጊዜ አብሮ ተከትሎ ክርስቶስ በስጋ እዚህ ምድር ለመምጣቱና ለመሞቱ እንዲሁም ከሙታን ለመነሳቱ ምስክር መሆን ስለሚያስፈልግ እና የተመረጡትም 12 ብቻ ስለሆኑ ማንም ይህን ቦታ ሊይዝ አልቻለም።



www.Ethiocross.com

እነዚያም በዲያብሎስ የተላኩ ሃሰተኛ ሃዋርያት ይፈታተኑ የነበሩት የነጴጥሮስን ሃዋርያነት ሳይሆን የጳውሎስን ሃዋርያነት እንደነበረ ከጳውሎስ መልእክቶችና ከጻፋቸው ጽሁፎች ልንረዳ እንችላለን። የአሁኑም ዘመን ሃዋርያት እንዲሁ እንደድሮዎቹ ሀሰተኛ ሃዋርያት ተከራካሪዎች ጳውሎስን ሆነው ሊገኙ ይፈልጋሉ። ከጽሁፎቻቸው እንደምንረዳውም ጌታ በስጋ ሆኖ ከማረጉ በፊት በምድር ላይ ሲያገለግል ሳለ ጳውሎስ አብሮት እንዳልነበረ ሁሉ እኛም እንዲሁ ከጌታ ጋር በስጋ አልነበርንም ፤ ነገር ግን ልክ እንደ ጳውሎስ መገለጥ ስላለን እኛም መሰረት ስለሆንን በመጽሃፍ ቅዱስ ከተጻፈውም ውጪ መገለጥ ብናመጣ ልትቀበሉን ይገባል ፤ ስለዚህ አድምጡን እያሉን ነው። ለመሆኑ ታላቁ የአህዛብ ሁሉ ሃዋርያ ጳውሎስ የተቀበለውን ጸጋና ስልጣን ይህን ያህል ቀላል አደረጉትን? እንደ እርሱስ መሰረት ሆነው ሊገኙ የሚፈልጉ እነዚህ ሃዋርያ ነን ባዮች በእውነት ባካሄድ ባረማመዳቸው እርሱንስ ይመስላሉን? በአብና በፍጥረት ሁሉ ፊትስ ስለ ጌታ ኢየሱስስ ትንሳኤ ምስክር ለመሆንስ ከትንሳኤ በኋላ ጌታ ኢየሱስንስ አይተውታልን? ለዚህ መልስ ሲሰጡ አንዳንዶቹ የዘመኑ ሃዋርያት አዎን አይተነዋል ይላሉ ፤ መገለጥ አይተናል ፤ ሰማይ ቤት ደርሰን ጌታን አይተን መጥተናል በማለት ዲያብሎስ እራሱ እንደብርሃን መልአክ መለወጥ እንዲችል የዘነጉቱን ለማታለል ይህን ይላሉ። ሃዋርያው ጳውሎስን ግን ጌታ መሰረት ሊያደርገው ሲያስብ የተገለጠለት በብርቱና በተለየ ሁኔታ እንደነበር ከጌታ ቃል ማስተዋል ይቻላል። ጌታ እራሱ ከሰማይ ወርዶ ታላቅን ስልጣንና ሃላፊነት ፤ የአህዛብ ሁሉ አስተማሪና ገላጭ ሊያደርገው እንደሃዋርያነቱ ደግሞ **የትንሳኤው ምስክር** እንዲሆን ሲመርጠው ፤ ይህ ሰው እስኪጸለይለት ድረስ ከጌታ ክብር የተነሳ ስጋዊ አይኑ ታውሮ ማየት እንዳልቻለ እናነባለን። ጌታም ለሃዋርያው ጳውሎስ ሲናገረው ከእርሱ ጋር በመንገድ የሄዱ ሰዎች ብርሃኑን በስጋዊ አይናቸው አይተው እንደፈሩ ፤ ደግሞም ድምጹን በስጋዊ ጆሮቻቸው ሰምተው ራሳቸው እንደዲዳዎች ሆነው እንደቆሙ ቃሉ ያስተምረናል (የሃዋርያት ስራ 9፡7 ፤ 22፡9) እንጂ የአሁኑ ሃዋርያት ሰማይ ቤት ደርሰን መጣን ወይም ተገለጠልን እንድሚሉቱ አይነት ማንም ተነስቶ ሊለው እንደሚችለው አይነት መገለጥ አልነበረም።

ደግሞም ከዚህ ባሻገር ለኛም ብርቱ ማረጋገጫ ይሆነን ዘንድ የጳውሎስን የሃዋርያነት ማእረግና ትምህርቱን እንድንቀበለው እንዲገባን ከነጴጥሮስና ከሌሎቹ ጌታን በስጋ ካዩቱ ሃዋርያት እንዲሁም ሽማግሌዎች ይህ ሰው ማረጋገጫ የተሰጠው ታላቅ የእግዚአብሄር ባሪያ ነው (የሃዋርያት ስራ ም.15)። በአሁኑ ሰአት ግን አዲስ የተሳሳተ መሰረት ለመመስረት ካልሆነ በቀር ፤ ያውም ከ 2000 አመት በኋላ ፤ አሁን ለቤተክርስትያን መሰረት ነን ለሚሉቱ የሚመሰክርላቸው አንድም የጌታ ሃዋርያ የለም ሁሉም በጌታ እረፍት ናቸውና። መቼም ሃዋርያው ጳውሎስ ተሳስቷል ካላልን በስተቀር ሌላ መስራች ሃዋርያ ከእርሱ በኋላ እንደሌለ የመጨረሻው እንደሆነ ሲነግረን በ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡7-8 እንዲህ ይላል።- “ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ ኋላም ለሐዋርያት ሁሉ ታየ፤ **ከሁሉም በኋላ** እንደ ጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየኝ።”

ወንድሞች ሆይ የእውነተኛው የእግዚአብሄር ቤት መሰረትስ ድሮ ገና በክርስቶስ ሃዋርያት ተጥሎ ከእነርሱ በኋላ እያንዳንዱ ክርስትያን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብሮ መሰረቱ ሳይለወጥ ፤ እንዲሁም ሳይጨመርና ሳይቀነስ ይህው እስካሁን ለእግዚአብሄር ቤት ለመሆን እየተሰራ ነው። ይሄ ግን አዲሱ ሃዋርያት መሰረት ነን የሚሉት ጉዳይ ብርቱ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል። ምክንያቱም የእግዚአብሄርን ቤት ሳይሆን ሌላ አዲስ ቤት በአዲስ መሰረት ላይ ሊሰሩ እየተጣጣሩ ስለሆነ ነው። እዚህ አዲስ ቤት ውስጥም እንደቃሉ ስላልተሰራ ጌታ እግዚአብሄር እንደማይኖርበት ግልጽ ነው። የሃዋርያት ስራ 11፡36 ላይ “ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና“ ይላል። እዚህ ጋር እንደምናየው ሁሉ በእርሱ ስለሚል ፤ በእርሱ ከሆነ ደግሞ እርሱ ማለትም ጌታ ከቃሉ ውጪ ባለ አሰራር ፈጽሞ ቤት እንደማይሰራ የታወቀ ነው።



www.Ethiocross.com

ሃዋርያው ጳውሎስ በ 1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ ም.3 እና ወደ ቲቶ ም.1 ላይ የቤተክርስትያን መሪዎች ማለትም የኤጲስቆጶሳት ፤ የሽማግሌዎችና የዲያቆናት መመዘኛ ምን እንደሆነ ይገልጻል። ነገር ግን ልብ ማለት ያለብን ቤተክርስትያንን የሚመሩ ከአሁን በኋላ ሃዋርያት ናቸው ፤ መመዘኛቸውም ይህ ነው ብለው ከእነርሱ በኋላ ስለሚነሱቱ አዲስ ሃዋርያትና መመዘኛቸው የትኛቹም የጌታ ሃዋርያት አልጻፉልንም።

የክርስቶስ ሃዋርያት ከሞቱ በኋላም ስላለው የቤተክርስትያንን ታሪክ ባጭሩ ብንመለከት ፤ ቀለሜንጦስ የተባለው በፊልጵስዩስ 4፡3 ላይ ሃዋርያው ጳውሎስ የጠቀሰው እንደሆነ የሚነገርለት ሰው[9] ፤ በቆሮንቶስ ስለተሾሙት ኤጲስ ቆጶሳት፡ ሽማግሌዎች እንዲሁም ዲያቆናት ጉዳይ በ 97 አ ም. በጻፈው ደብዳቤ ላይ ክርስቶስ በአብ ተልኮ ለሃዋርያቱ የወንጌል መስራችነት ስልጣን እንደሰጣቸው ፤ ሃዋርያቱ እራሳቸው ደግሞ ክርስቶስ በአብ እንደተላከ እነርሱ ደግሞ በክርስቶስ ተልከው የመጨውን ትውልድ ቤተክርስትያን የሚመሩት ኤጲስ ቆጶሳት ፤ ሽማግሌዎችና ዲያቆናትን እንደሆኑ በጽሁፉ ይገልጻል[10]። ቀለሜንጦስም ቤተክርስትያንን የሚመሩት ሃዋርያት እና ነቢያት ናቸው አላለም። ይህም የቀለሜንጦስ ጽሁፍ ደግሞ ከሀዋርያቱ በኋላ የተነሡት የእምነት አባቶች ስለቤተክርስትያን አመራር መጽሃፍ ቅዱስ የሚናገረውን ምን ያህል በብርቱ ሲከተሉ እንደነበረ ያሳየናል።

በተጨማሪም ሪፎርሚስቶቹ እነ ማርቲን ሉተርም ቢሆኑ sola scriptura "መጽሃፍ ቅዱስ ብቻ" በማለት ከተጻፈው ሳያልፉ ፤ መሰረት ነን ሳይሉ ፤ ያሳዩን የነበረው እንደዘመኑ ሃዋርያት እራሳቸውን ሳይሆን ፤ ታላቁን ንጉስና ፤ የመዳን መንገዱን እርሱም ጸጋውን ነበር። እስከሞትም ድረስ ለተጻፈው ነገር እራሳቸውን የሰጡ ጀግኖች ነበሩ እንጂ አዲስ ነገር አሾልከው ሊያስገቡ የሞከሩ ሰዎች አልነበሩም።

እንግዲህ የጌታን ቃል ፤ እንዲሁም እንደ እነዚህ በታሪክ የተመሰከረላቸውን የእምነት አባቶች ያቆሙትን መሰረት ጥሰን ብንሄድ በመጽሃፈ ምሳሌ የተጻፈው አባቶችህ የሠሩትን የቀድሞውን የድንበር ምልክት አታፍልስ። ቅጥርንም የሚያፈርስን እባብ ትነድፈዋለች (መጽሐፈ ምሳሌ ም. 10 እና ም. 22) የሚሉት የጌታ ቃላት ይፈርዱብናል። ምነው በዚህ የትውልድ ታሪክ ማጠቃለያ በሆነበት በአሁኑ ዘመን በብዙ ጥንቃቄ ልንኖር ሲገባን እንዲህ አይነት መገለጥ ይዞ መነሳት ለምን አስፈለገ? ነው ወይስ የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት **ክህደት** እንደሚኖር ከዚያም የአመጽ ሰው እንደሚገለጥ ቀድሞ የተነገረን ቃል አይናችን ፊት እየተፈጸመና ሊፈጸም ይሆንን? (2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2፥3 ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ፤ **ክህደቱ** አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ፥ አይደርስምና።) እነዚህ አዲስ ሃዋርያት መሰረት ነን ስለሚሉ ፤ መጽሃፍ ቅዱስን እንደመጨረሻ መገለጥና እንደመጨረሻ ስልጣን አያከብሩትም እንዲያውም ይንቁታል እንጂ።

ለነገሩ ይህ ትምህርት እንደሰሙ አዲስ ሳይሆን እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር በ1940ዎቹ በተለይ በአሜሪካን አገር ሲያምስ የነበረውን የኋለኛውን ዝናብ (Latter Rain) ትምህርት ለማንሰራራት የሚደረግ በሃይልና በፍጥነት እየተሳካለት ያለ ፊጣን ፤ ታላቅና አስፈሪ እንቅስቃሴ ነው። በዚህ እንግዳ ትምህርት የተቸገሩት የአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ (Assemblies of God) ቤተክርስትያናት በ 1949 በሲያትል (አሜሪካ) በተደረገው ጠቅላላ ጉባኤአቸው ላይ ካወገዙአቸው የተለያዩ አሰራር መካከል በሁለተኛ ተራ ቁጥር ላይ የዘመኑ ሃዋርያትና ነቢያት የቤተክርስትያን መሰረት እንዳልሆኑ የሚገልጸው ጽሁፍ እንዲህ ሲል ሰፍሩአል፡ "The erroneous teaching that the church is built on the foundation of present-day apostles and prophets[11] "ቤተክርስትያን የተመሰረተችው በአሁኑ ዘመን ባሉ ሃዋርያቶች እና ነቢያት ላይ ነው የሚለው ትምህርት የተሳሳተ ነው" በማለት



www.Ethiocross.com

ይህንን በአሁኑ ዘመን መሰረት ነን የሚለውን የአዲሶቹን ሃዋርያት ትምህርት የአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ቤተክርስትያናት ከኮነኑትና ካወገዙት 60 አመት አልፎታል። አሁንም እዚህ ጋር በድጋሚ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ቤተክርስትያናት መሪዎች ተነስተው ይህንን እንግዳ ትምህርት ጥፋቱ ሳይበዛና ባያሌው ስር ሳየሰድ ባስቸኳይ እንዲኮንኑ በክርስቶስ ፍቅር እለምናለሁ።

የእነዚህ የአዲሱ ሃዋርያት አይነትም ብዙና ቁጥር ስፍር የሌለው ነው። አንዱም አይነት እንኳን በመጽሃፍ ቅዱስ አለተጠቀሰም። ጥቂቱን እዚህ ጋር በ እንግሊዝኛው ቋንቋ እነርሱው እራሳቸው እንደሚጠሩበቱ እንዘረዝራቸዋለን፤ Horizontal apostle, Vertical Apostle, Hyphenated Apostle, Market Place Apostle - እነዚህ ደግሞ በመቀጠል - Apostles of finance, Apostles of Technology, Apostles of medicine, Apostles of Industry, Apostles of Education, Apostles of business……[12] እያለ ዝርዝሩ ይቀጥላል። ስለ እያንዳንዱ ሃዋርያ አይነት ግን እዚህ ጋር መዘርዘር ለጊዜው ተገቢ አይመስለኝም። ሌላውን ትምህርታቸውንና አላማቸውን ደግሞ እስኪ ቀጥለን እንመልከት፦

## የአዲሱ ሃዋርያት እንቅስቃሴ አላማ

2. የእነዚህ የአዲሱ ሃዋርያት እንቅስቃሴ አላማ ባጠቃላይ በምድር ላይ ማህበረሰባዊ ለውጥ ማምጣት ነው። ቀላሉንና ቀጥተኛውን የጌታን ወንጌል ሰዎች ቢቀበሉትም ባይቀበሉትም መስበክ ብቻ ሳይሆን ይህ እንቅስቃሴ ከአዲሶቹ በዘመኑ ካሉ መሰረት ነን ከሚሉ ነቢያት ጋር ክርስትናን ብቻ ሳይሆን ምድርን በሙሉ ለመቆጣጠር ነው። የምድርን ሁሉ ሃይላት (በሮች፤ ተራሮች እንዲሁም ጎራዎች በማለት የሚጠሯቸውን) በሰባት ከፍለው እነዚህን ሰባት ታላላቅ ተራሮች ለመቆጣጠር ሃዋርያቱ ከነቢያቱ ጋር ታጥቀው ተነስተዋል። እነዚህ ሰባት የምድር ላይ ተራሮች በሃዋርያቱ መሪ በ ዶ/ር ፒተር ዋግነር አገላለጽ መሰረት[13]፤

- ሀ. ሃይማኖት - Religion
- ለ. ቤተሰብ - Family
- ሐ. ሀገር አመራር - Government
- መ. አርት እና መዝናኛ - Arts and entertainment
- ሠ. የዜና አውታሮች - The media
- ረ. ንግድ - Business
- ሰ. ትምህርት - Education ናቸው።

በመቀጠልም እዛው ገጽ ላይ ዶክተሩ እንዲህ ይላሉ። It should be obvious to anyone that for society as a whole to change, each one of these molders of culture needs to be led or "dominated"….. My hope is that those who agree with God's standards of human life will be those individuals who, at the end of the day are in positions to have dominion over society, whether it be within cities or states or nations or other territories.
"ለማንኛውም ሰው ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ ማህበረሰብ ባጠቃላይ ለመለወጥ ፤ እያንዳንዱን ማህበረሰቡን የሚለውጡትን እነዚህን ሃይላት መምራት ወይም መቆጣጠር ያስፈልጋል። … ተስፋ የማደርገውም በመጨረሻው ላይ ከተማንም ቢሆን፤ ክልልንም ቢሆን፤ ወይም ሃገርንና ግዛታትን የሚገዙና የሚቆጣጠሩ ሰዎች እግዚአብሄር ስለሰው ልጅ ህይወት ያለውን መስፈርት የሚቀበሉና የሚስማሙ እንዲሆኑ ነው"።

እዚህ ጋር በግልጽ እንደምናየው የእነዚህ ሃዋርያት አላማ ክርስትያኑንና ቤተክርስትያንን ብቻ ሳይሆን አለምንም ጭምር መምራትና መቆጣጠር ነው። ነገር ግን መንግስቱ ከዚህ ምድር



www.Ethiocross.com

አይደለችምና በዚች ምድር ላይ አንዳያነግሱት ስለ ጌታ ኢየሱስ ስለ እራሱ እንዲህ ሲል ተጽፏል "... ኢየሱስ ያነግሡት ዘንድ ሊመጡና ሊነጥቁት እንዳላቸው አውቆ ደግሞ ወደ ተራራ ብቻውን ፈቀቅ አለ" (የዮሐንስ ወንጌል 6፥15) ይላል። በተጨማሪም እውነተኛዎቹ የጌታ ሃዋርያት እራሳቸው ፤ እንኳን ምድርን ሊገዙና ሊሰለጥኑባት ይቅርና ፤ እንደሃዋርያው ጳውሎስ አባባል የዓለም ጥራጊ፤ የሁሉም ጉድፍ ፤ የሚራቡ፤ የሚጠሙ ፤ የሚራቆቱ ፤ የሚንከራተቱ (1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ም፡ 4) ነበሩ ። በሌላ ቦታም ምሳሌ የሚሆኑንን የእምነት አባቶችን የእብራውያን ጸሃፊ ሲዘረዝር ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ፥ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ (ወደ ዕብራውያን 11፥38) እንጂ በአለም ላይ ሰልጥነውባትና ነግሰውባት አለፉ ወይም ያልፋሉ የሚል ትምህርት የጌታ ሃዋርያት አላስተማሩንም። ስለዚህ እነዚህ አዲስ ሃዋርያት ወዴት ሊወስዱን እያሰቡ እንዳሉ ወገኖች ሆይ እናስተውል። እንዴትም ከቃሉ ውጪ አዲስ መሰረት እየመሰረቱም ደግሞ እንዳሉ ልብ እንበል።

እነዚህ የአዲሱ ሃዋርያት እንቅስቃሴ አባላት ወደ ህይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ የሚያገኙትም ጥቂቶች እንደሆነ ይሚናገረውን ቃል እየጣሱ፤ (ማቴዎስ 7፡14) በሁሉም ዘንድ ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል የሚለውን ቃል እየጣሱ (ማርቆስ 13፡13)፤ የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆንን? (ሉቃስ 18፡8) የሚለውን የጌታችንን እይታ ፤ ማለትም የሰው ልጅ በመጨረሻው ዘመን እምነቱ እንደሚመነምን የሚናገረውን ቃል እየጣሱ፤ ተቃራኒውን የሚያስተምሩ ሰዎች ናቸው። እነዚህ መሰረት አፍራሾች ሊያጠፉን ፤ ከተመሰረተውና በቃሉ ከተማርነው ውጪ አዲስ መሰረት የሚመሰርቱ ፤ የታላቁንና የተፈራውን የጌታችንን ቃል የሚንቁ ፤ ነገር ግን ከቃሉ ይልቅ የራሳቸውን መንፈስና አጋንንትን የሚያደምጡ ፤ ስልጣንና ገንዘብ እንደውሃ የጠማቸው ሀሰተኛ ሃዋርያት ናቸው።

"በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ" (2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥12) የሚለውን ቃል ትተው እነዚህ ስለክርስቶስ ወንጌል እንዳይሰደዱ ነገር ግን ስለጌታ ሲሉ ሁሉን ትተው መከተልና መንከራተት የማይፈልጉ ፤ እውነተኛ ሃዋርያትስ ቢሆኑ ኖሮ ፤ በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ከተማና ክልል እየከፋፈሉ ለመግዛት ከሚያስቡ ይልቅ ፤ የጌታ ቃል እስረኞችና ባሮች ሆነው መልካሙን መንገድ ፤ ያውም የመስቀሉን መንገድ ባሳዩን ፤ ለእኛም ምሳሌና ብርታት በሆኑ ነበር።

ነገር ግን ማርቆስ 10፡ 42-43 ላይ "ኢየሱስም ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፦ የአሕዛብ አለቆች ተብሎ የምታስቡት እንዲገዙአቸው ታላላቆቻቸውም በላያቸው እንዲሠለጥኑ ታውቃላችሁ" ይልና በመቀጠል እዛው "በእናንተስ እንዲህ አይደለም" ይላል። እነዚህ ግን ጌታ የሚለውን ቃል ንቀው እንደአህዛብ አለቆች እዚሁ በምድር ላይ የሰው ልጅ ላይ ሰልጥነው እዚሁ ዋጋቸውን የሚቀበሉ ፤ ብዙዎችን ገና የሚያስቱ ፤ ከክፉው መንፈስ ጋር አለሙንና ቢቻላቸው የተመረጡትንም ሊያስቱ የወጡ ፤ ራሳቸውን እንደ ክርስቶስ ሃዋርያት የለወጡ የበግ ደምና ስጋ የጠማቸውና የራባቸው ተኩላዎች ናቸው።

ለዚህ ለተነሱበት ታላቅ አላማ ደግሞ የአለም ሁሉ ገንዘብ በእጃቸው መግባት ስላለበት ይህንንም ገንዘብ የሚያስገቡበትን አሰራር market place apostles የሚሏቸውን ሃዋርያት የምድርን ሃብት ወደ እጃቸው እንዴት እንደሚያስገቡ የሚያስተምሩበትንና የሚያሰለጥኑበትን ድረ-ገጽ http://www.kingdomeconomicsummit.com/videos.html በሚለው ይመልከቱ።



www.Ethiocross.com

መሪያቸው ዶ/ር ፒተር ዋግነር ደግሞ ስለገንዘብ Dominion! በሚለው መጽሃፋቸው ላይ እንዲህ ይላሉ፦ A new Influence - Money Answers Everything. If you check back through human history, you will find that three things, more than any others, have produced social transformation: violence, knowledge and wealth — and the greatest of these is wealth! [14] "አዲስ መፍትሄ - ገንዘብ ለሁሉ ነገር መልስ ይሆናል። የሰው ልጅችን ታሪክ ዞር ብለን ብንመለከት ማህበረሰብን ለመለወጥ ከሁሉም በላይ ሶስት ነገሮች ተጽእኖ ያደርጋሉ ፤ ንጥቂያ ወይም ረብሻ ፤ እውቀት እና ሃብት ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ከሁሉ የሚበልጠው ሃብት ነው"::

ስለዚህ እነዚህ ሰዎች አላማቸው ከላይ እንዳየነው ሁሉን ነገር በቁጥጥራቸው ስር ማዋል ነው ፤ ገንዘብና ሃብት ሳይቀር። ስለዚህ የምድርን ስጋዊ ሃብትና ንብረት ለመቆጣጠር በሚያደርጉት አካሄድ ላይ መቼም ምንም አይነት ማብራሪያ የሚያስፈልገው አይመስለኝም እራሱ በራሱ በብዙ ስለማንነታቸው ያሳያልና። የክርስቶስ ሃዋርያ ግን በሃዋርያት ስራ 3፡6 ላይ እንዲህ አለ፦ "ጴጥሮስ ግን። ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው።" እነዚህ የአዲሱ ዘመን የቤተክርስትያን ሃዋርያትና መሰረት ነን ባዮች በአኗኗርም ሆነ በአላማ ከቀደሙቱ ከክርስቶስ ሃዋርያት ጋርም ሆነ ከቀደሙቱ ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ጋር በፍጹም አይገናኙምም አይመሳሰሉምም። አዲስን ወንጌል በአዲስ መሰረት እየሰበኩልን ነው። እንግዲህ የምንከተላቸውን ሃዋርያት መምረጥ ሊያስፈልገን ግድ እየሆነ ነው።

ጌታ በግለሰቡ ላይ ነግሶ ፤ ቃሉ ተከብሮ እንዲሁም ሳይቀየርና ሳይሸቃቀጥ ማህበረሰብን በብዛት ወደ ክርስትና ለመቀየር እና ምድርን ለመቆጣጠር የሚደረግ እንቅስቃሴ ፤ እንደማይዛልቅ ከታሪክ መማር እንችላለን። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ይህንን አካሄድ ፤ የከበሩትና በምድር ላይ እንደ ተፈተነ ፤ ሰባት ጊዜ እንደ ተጣራ ብር የነጹት የእግዚአብሔር ቃላት እንደማይደግፉት (መዝ 12፡6) እያዩ እንዴት እነዚህ የአዲሱ ሃዋርያ እንቅስቅሴ መሪዎች ወደዛ ቃሉም ታሪክም ወደማይደግፈው አካሄድ መልሰው ክርስትያኑን ሊወስዱ ያስባሉ? ነው ወይስ እግዚአብሄር መቼም ዓይዘበትበትምና ፍርድም ከጌታ ቤት ይጀምራልና ፤ ይልቅስ ለእነዚህ ለአስተማሪዎች ለነፍሳቸው ምኞት (የስልጣን ፤ የገንዘብ ጥም) ፤ ለእኛ ለምእመኑ ደግሞ እውነትን መስማት ጆሮአችንን የሚያሳክክንና የማይጥመን ስለሆነ (2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡3) እንደነዚህ ያሉትን በሃይለኛ ታክቲክ እየተቀነባበሩ የሚመጡትን መሰረት አፍራሽ የሆኑትን ትምህርቶች ተቀብለን እንድናስተናግድ እግዚአብሄር እንዲህ የመሰሉትን ሃይለኛና ስወር ደባ እድናምነው እየላከብን ይሆንን? "ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል" (2 ተሰሎንቄ 2፡11-12) ። በሌላም ቦታ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ ይል የለ (ማቴዎስ 24፡24) ። ጌታ እግዚአብሄር ግን እርሱን የሚወዱትን ከዚህ በመጨረሻው ዘመን ከወረደ አዚም ይጠብቅ አሜን።

## የአዲሱ ሃዋርያት እንቅስቃሴ የመጽሃፍ ቅዱስ ትምህርት

**3.** የዚህ እንቅስቃሴ የመጽሃፍ ቅዱስ ትምህርት እይታ ዶሚኒየን ቲኦሎጂ (Dominion Theology – Kingdom Now Theology) በመባል ይታወቃል[15]:: የእንቅስቃሴው መሪ ዶ/ር ፒተር ዋግነር Victorious Eschatology በሚለው መጽሃፍ በጻፉት መግቢያ ላይ እንዲህ ይላሉ። When I first read Victorious Eschatology, a light bulb went on in a dim part of my brain! Since I have become a strong advocate of dominion theology[16]. "ለመጀመሪያ ጊዜ ቪክቶሪየስ ኤስካቶሎጂ የተባለውን መጽሃፍ ሳነብ ጨለም ባለው የአእምሮዬ ክፍል ውስጥ ብርሃን እንደበራልኝ ያህል ተሰማኝ ! ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የዶሚኒኦን ቲኦሎጂ ሀይለኛ አራማጅ



www.Ethiocross.com

ሆንኩኝ።" በተጨማሪም በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ ያየናቸው የመጽሃፍ ቅዱስ አስተምህሮአችውንና በገሃድ በቅርቡም እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር ዶክተሩ በ 2008 ያሳተሙትን Dominion! – How Kingdom Action Can Change The World የሚለውን መጽሃፋቸውን በማንበብ አንባቢው ስለዚህ Dominion Theology/Kingdom Now ቲዎሎጂ ትምህርት በቂ ግንዛቤ ማግኘት ይችላል ብዬ አገምታለሁ። ሆኖም የዶሚኒኦን ቲኦሎጂ ትምህርቶች ቢመሳሰሉም በመካከላቸው ትንሽ ልዩነት ስላለ ማትኮር የፈለግኩበትን የአዲሱን የሃዋርያትና የነቢያት እንቅስቅሴ የዶሚኒኦን ቲኦሎጂ አይነት ፤ ከእነርሱው መሪዎች ጽሁፎች በመነሳት ከላይ የተዘረዘሩትን የእምነት እይታቸውን ለማቅረብ ሞክሬአለሁ። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ከዶሚኒኦን ቲኦሎጂ ጋር እጅና ጓንት ሆኖ ያለውን የመጨረሻው ዘመን እይታ እነርሱው እንደሚሉት እናያለን።

እንደ እንቅስቃሴው መሪ ዶ/ር ፒተር ዋግነር እምነት መሰረት የመጨረሻው ዘመን እይታቸው ፓርሻል ፕረተሪዝም (Partial Preterism)[17] የሚባለው ሲሆን ፤ እንዲህ አይነት እምነት ያላቸው ሰዎች በዳንኤል መጽሃፍ ፤ በማቴዎስ ወንጌል ምእራፍ 24-25 እና በዮሃንስ ራእይ ላይ የተነገሩት ትንቢቶች በአብዛኛው ተፈጽመዋል የሚሉ ናቸው። ለምሳሌ ሃሰተኛው ክርስቶስ መጥቶ ሄዷል፤ ስለዚህ ዶ/ር ፒተር ዋግነርና ይህንን ትምህርት የሚያራምዱቱ ሀሰተኛ ክርስቶስ ይመጣል ብለው ከአሁን በኋላ አይጠብቁም።

በመቀጠልም ስለመጨረሻው ዘመን ትምህርታቸው የራሳቸው ሃዋርያና-ነቢይ የሆኑት ቢል ሃመን እንዲህ ይላሉ God is preparing His Church to become an invincible, unstoppable, unconquerable, overcoming Army of the Lord that subdues everything under Christ's feet.[18] "እግዚአብሄር ቤተክርስትያኑን የማይፈርስ ፤ የማይሸነፍ ፤ እንዲሁም የማይበገር ሁሉን በክርስቶስ ስር የሚያስገዛ **የጌታ ሰራዊት** እያደረገውና እያዘጋጀው ነው"።

በእነዚህ በአዲሱ ሃዋርያትና ነቢያት የሚመራው ታላቅ **የጌታ ሰራዊት** የተባለው መጀመሪያ ሁሉን ነገር ለጌታ ኢየሱስ እስካላዝገዛለት ድረስ ጌታ ወደምድር ተመልሶ ሊመጣ እንደማይችል ይናገራሉ። ጌታ ምድር ላይ ሊነግስ ከመምጣቱ አስቀድሞ መገዛት ካለበት ነገርም አንዱ ሞት ነው። ቢል ሃመን በመቀጠልም እንዲህ ይላሉ፦ There are millions of redeemed saints that have an end-time destiny to overcome death by participating in Christ's translation of His saints[19] "ሞትን ድል ለማድረግ በክርስቶስ የሚለወጡ ፤ በመጨረሻው ዘመን የሚገለጡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቅዱሳን አሉ።"

## በመጨረሻ

እንግዲህ በተወሰነ ወቅት ላይ የነዚህ የመጨረሻ ዘመን **ታላቅ የጌታ ሰራዊት** የሚሏቸው ሰዎች ሰውነት ወደማይሞት ሰውነት ሆኖ ይለወጣል ፤ ከዛ ጌታ እስኪመጣና ያዘጋጁለትን እስኪወርስ ድረስ እነዚህ የማይሞቱ ሰዎች ሁሉን ነገር ከእግሩ ስር ያስገዙ ዘንድ ብዙ ታላላቅ ነገሮችን በምድር ላይ ያደርጋሉ። ንጥቀትም እንደሌለ ፤ ማለትም ክርስትያኖች ከዚህ ምድር ተነጥቀው እንደማይሄዱ ያስተምራሉ።



www.Ethiocross.com

## ማሳሰቢያ

---

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ አንባቢው ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው በማለት አንዳንድ ቃላት ወይም ሃረጎች ከለሎቹ በተለየ ሁኔታ ጎላ ተደርገው ቀርበዋል።

## ማስታወሻ

---

[1] C. Peter Wagner , 2008: Dominion! How Kingdom Action Can Change the World. Chosen, Grand Rapids Michigan, 222pp. – Refer. page 22.
[2] C. Peter Wagner, 2000: Apostles of the City – How to Mobilize Territorial Apostles for City Transformation, Wagner Publications, 60 pp. Refer. Page-46
[3] Ibid. p.44.
[4] Ibid. p54
[5] C. Peter Wagner, 2000: Apostles and Prophets - The Foundation of the Church, Regal, Ventura, California, USA, 144 pp. Refer p.69.
[6] Ibid. p49.
[7] C. Peter Wagner, 2000፡ Apostles of the City. op.cit. p14.
[8] Bill Hamon. 1997: Apostles Prophets and the Coming Moves of God – God's End-Time Plans for His Church and Planet Earth. Destiny Image Publishers Inc., Shippensburg, PA., 299pp. Refer. p140.
[9] DeWaay B. , 2007: The roots and Fruits of the New Apostolic Reformation. Critical Issues Commentary, Issue Number 103. November/December 2007.
[10] Roberts, Alexander ; Donaldson, James ; Coxe, A. Cleveland, 1997 : The Ante-Nicene Fathers Vol.I : Translations of the Writings of the Fathers Down to A.D. 325. Oak Harbor : Logos Research Systems, S. 16; First Epistle of Clement to the Corinthians chapter 42 and 44.
[11] William W. Menzies, 1971: Anointed to Serve: The Story of the Assemblies of God. Springfield, Mo.: Gospel Publishing House. 436 pp. Refer p.325.
[12] C. Peter Wagner, 2000: Apostles and Prophets. Op.cit. p. 42-55
[13] C. Peter Wagner , 2008: op.cit. p.12.
[14] Ibid. p 181
[15] Ibid. p 12
[16] Harold R. Eberle & Martin Trench, 2007: Victorious Eschatology, A Partial Preterist View, Worldcast Publishing, 337pp.
[17] C. Peter Wagner , 2008. op.cit p 61-62.
[18] Bill Hamon op.cit p.251
[19] Ibid. p265.

**ጥያቄ ወይም ሃሳብዎን ለፀሐፊው ለማካፈል ከፈለጉ በሚከተለው ኢ-ሜይል መላክ ይችላሉ** **ዶ/ር ቴዎድሮስ አየለ contact@kendemeleket.com**



www.Ethiocross.com